መልእክት ስድስት

**በዘመኑ አገልግሎት መሠረት**
**የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ ኢኮኖሚ ከፍተኛ ወንጌል**
**የዳበረ እውነት ማወቅና ማሰራጨት**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ 2 ጴጥ. 1፡12፤ 1 ጢሞ. 1፡3-4፤ ማቴ. 16፡18፤ 2 ሳሙ. 7፡12-14፤ ሮሜ 1፡3-4፤ ራእ. 21፡2፣ 9-10

I. **በአንድ ዘመን ውስጥ እግዚአብሔር እያደረገ ያለው ልዩ የሆነ ምለሳ እና ሥራ የዚያ ዘመን አገልግሎት ነው፤ የዘመኑ አገልግሎት የጊዜውን እውነት ለእግዚአብሔር ሕዝብ ያገለግላል፤ በ 2ኛ ጴጥሮስ 1፡12 *በእናንተም ዘንድ ባለ እውነት* የሚለው ቃል "የአሁኑ እውነት" ተብሎ ሊተረጎም ይችላል፦**

ሀ. ምንም እንኳን ሁሉም እውነቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ቢኖሩም፣ በሰው ሞኝነት፣ ታማኝ አለመሆን፣ ቸልተኝነት እና አለመታዘዝ ብዙ እውነቶች ጠፍተዋል፣ ከሰውም ተሰውረዋል—ተዛ. 2 ነገ. 22፡8።

ለ. የተገለጡ ትኩስ እውነቶች የእግዚአብሔር አዲስ ፈጠራዎች አይደሉም፤ ይልቁንም የሰው አዲስ ግኝቶች ናቸው፤ እያንዳንዱ የጌታ ሠራተኛ የአሁኑ እውነት ምን እንደሆነ እግዚአብሔርን መጠየቅ አለበት።

ሐ. የእግዚአብሔር እውነቶች እየጨመሩ የሚያድጉ ናቸው፤ ኋላ የሚገለጡ እውነቶች የቀደሙትን አይቃረኑም፤ ዛሬ የምናያቸው የእግዚአብሔር ያደጉ መገለጦች ናቸው።

መ. "ከጊዜው እውነት" አኳያ ወደኃን የተጣልን ሰዎች እንዳንሆን እግዚአብሔር ቸርነቱን ያሳየን፤ የነቃን እና ሥጋ ሰርጎ እንዲገባ ወይም እኔነት ምንም ሥፍራ እንዲያገኝ የማንፈቅድ እንሁን።

II. **በዘመኑ አገልግሎት በኩል በእግዚአብሔር ለእኛ የተሰጠን የጊዜው እውነት፣ የመለኮታዊው መገለጥ ከፍተኛ ጫፍ የእግዚአብሔር ዘላለማዊው ኢኮኖሚ መገለጥ ነው፤ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ ወንጌል—"ለአባቶች የተሰጠው ተስፋ የምስራች" (ሐዋ. 13፡32)—የዳዊት ዘር የእግዚአብሔር ልጅ የሚሆንበት ተስፋ፣ ማለትም፣ የሰው ዘር መለኮታዊ ዘር እንደሚሆን የተነገረበት—ነው (ቁ. 22-23፣ 33-34፤ 26፡6፣ 16-19፤ 2 ሳሙ. 7፡12-14፤ ሮሜ 1፡3-4፤ ማቴ. 22፡41-45)፦**

ሀ. የሰዎችን ይረዱታል ብለን ወደ ምናስበው ደረጃ ዝቅ የተደረገ ወንጌል መስበክ የለብንም፤ ከፍ ያለውን ወንጌል መስበክ አለብን፣ ጽንሰ-ሃሳቡንም ፈጽሞ ማሳነስ የለብንም (1 ተሰ. 1፡1፣ 3-4፣ 10፤ 5፡23፤ 1 ቆሮ. 2፡7-13)፤ የእግዚአብሔርን ነገሮች መቀበል እና መረዳት የሚችል በእግዚአብሔር-የተፈጠረ ችሎታ በሰው ውስጥ እንዳለ የግድ ማመን አለብን (ኢዮ. 32፡8፤ ዘካ. 12፡1፤ መክ. 3፡11፤ ሐዋ. 17፡26-29፤ ኢሳ. 43፡7)።

ለ. የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ ኢኮኖሚ የሚመለከተውን እውነት በመላው መጽሐፍ ቅዱስ መሠረት በዓይነት በዓይነቱ ማቅረብ አለብን፣ ይህ ለእኛ የጌታ ልዩ ተልዕኮ ነው—1 ቆሮ. 1፡9፤ 9፡16-17፣ 23፤ 1 ጢሞ. 1፡3-4፤ 2፡7፤ 4፡16፤ 2 ጢሞ. 1፡11፤ 2፡2፣15፤ ቆላ. 1፡28።

III. ***የዳዊት ዘር የእግዚአብሔር ዘር መሆኑ* ክርስቶስ በትንሣኤ የእግዚአብሔር በኩር ልጅ ሆኖ ስለተሰየመበት ሂደት ይናገራል—ሮሜ 1፡3-4፦**

ሀ. ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ልጅ ስለሚመለከተው ወንጌል እንደተለየ ተናገረ፣ ይህም የእግዚአብሔር ወንጌል ለክርስቶስ አካል እውነታ የልጅነት ወንጌል እንደሆነ ያመለክታል—ቁ. 1፡3-4፤ 8፡28-30፤ 12፡5።

ለ. ተመላኪነቱን ሳይጨምር በሕይወት እና በባሕርይ ሰው አምላክ ይሆን ዘንድ አምላክ ሰው የመሆኑን ምሥጢር በመግለጥ ሮሜ 1፡3-4 በ 2ኛ ሳሙኤል 7፡12-14 በምሳሌ የተቀመጠው ትንቢት መፈጸም ነው።

ሐ. በመለኮትነቱ የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ (ዮሐንስ 1፡18) የሆነው ክርስቶስ በተሠግዎ ከመለኮትነት ጋር ምንም ግንኙነት የሌለውን ሥጋ፣ የሰውን ተፈጥሮ ለበሰ፤ በስብዕናው የእግዚአብሔር ልጅ አልነበረም።

መ. በትንሣኤ ስብዕናው መለኮት፣ ልጅ ተደረገ፣ ማለትም በስብዕናው የእግዚአብሔር የበኵር ልጅ በመሆን እና መለኮትነትን እና ስብዕናን በመያዝ የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ተሰየመ—ሮሜ 8፡29።

ሠ. ስለዚህ፣ እግዚአብሔር በክርስቶስ ወደ ሰው ውስጥ ተቀናበረ፣ ሰው ወደ እግዚአብሔር ውስጥ ተቀናበረ፣ እግዚአብሔር እና ሰው አንድ አካል፣ አምላክ-ሰው ለመሆን በአንድ ላይ ተዋሐዱ።

ረ. በኢኮኖሚው የእግዚአብሔር ወንጌል እና የእርሱ ውጥን እግዚአብሔርን ወደ ሰው ውስጥ መገንባት እና ሰውን ወደ እግዚአብሔር ውስጥ መገንባት ናቸው፤ ይህ ግንባታ ሰው አምላክ (የተሰየመው የእግዚአብሔር ልጅ) ይሆን ዘንድ አምላክ ሰው (የዳዊት ዘር) መሆኑ ነው—ዮሐ. 14፡23፤ 15፡4-5፤ ሮሜ 1፡3-4።

ሰ. ይህ ወንጌል በጌታ ኢየሱስ “እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ የስንዴ ቅንጣት በምድር ወድቃ ካልሞተች ብቻዋን ትቀራለች፤ ብትሞት ግን ብዙ ፍሬ ታፈራለች” ተብሎ ተነግሯል—ዮሐ. 12፡24፦

1. ዘር በአፈር ውስጥ በመቀበር ከሞተ በመጨረሻ በትንሣኤ ይበቅላል፣ ያድጋል እናም ያብባል፣ ምክንያቱም የዘሩ ሕይወት ሥራ የሚነሳሳው ከሞቱ ጋር በተመሳሳይ ጊዜ ነውና—1 ቆሮ. 15፡36፤ 1 ጴጥ. 3፡18።
2. በክርስቶስ ያለው መለኮትነት፣ የቅድስና መንፈስ በሞቱ የሚሠራ ሆነ፣ በትንሣኤም እኛን ብዙ ወንድሞቹ ያደርገን ዘንድ መለኮታዊ ሕይወቱን ወደ ውስጣችን በማካፈል የእግዚአብሔር የበኩር ልጅ እና ሕይወት-አዳይ መንፈስ ለመሆን ክርስቶስ “አበበ”—ሮሜ 8፡29፤ 1 ቆሮ. 15፡45።
3. የማራቢያ ሞዴሉ የእግዚአብሔር የበኩር ልጅ ነው፣ ርቢው ደግሞ በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም የሚጠናቀቀው አካሉ ለመሆን ብዙዎቹ የእግዚአብሔር ልጆች፣ የማራቢያው ሞዴል ብልቶች ነው—ቆላ. 1፡18፤ 1 ጴጥ. 1፡3።

## IV. የዳዊት ዘር የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑ በትንሣኤ የእኛን የእግዚአብሔር ብዙ ልጆች ተደርጎ የመሰየም ሂደት ይናገራል—ዕብ 2፡10-11፦

ሀ. ክርስቶስ እንደ የእግዚአብሔር ልጅ ተሰይሟል፣ እኛ ግን አሁንም በመሰየም ሂደት ውስጥ፣ ልጅ በመደረግ፣ መለኮት በመደረግ ሂደት ውስጥ ነን—ሮሜ 8፡28-29።

ለ. የእግዚአብሔር ልጅ ሕይወት ወደ መንፈሳችን ውስጥ ተተክሏል—ቁ. 10፦

1. አሁን እኛ፣ ወደ አፈር ውስጥ እንደተዘራ ዘር በሞት እና በትንሣኤ ሂደት ውስጥ ማለፍ አለብን—ዮሐ. 12፡24-26።
2. ይህ የውጭው ሰው እንዲጠፋ ያደርጋል፣ የውስጡ ሕይወት ግን እንዲያድግ፣ እንዲዳብር እና በስተመጨረሻም ከውስጣችን እንዲያብብ ያደርጋል፤ ይህ ትንሣኤ ነው—1 ቆሮ. 15፡31፣ 36፤ 2 ቆሮ. 4፡10-12፣ 16-18።

ሐ. በትንሣኤ ክርስቶስ በሰብዕናው የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ተሰየመ፣ በእንደዚህ አይነቱ ትንሣኤ እኛም የእግዚአብሔር ልጆች ሆነን በመሰየም ሂደት ውስጥ ነን—ሮሜ 8፡11፦

1. የመሰየማችን፣ ልጅ የመደረጋችን፣ መለኮት የመደረጋችን ሂደት ከአራት ዋና ገጽታዎች ጋር የትንሣኤ ሂደት ነው—መቀደስ፣ መለወጥ፣ መምሰል እና መክበር—6፡22፤ 12፡2፤ 8፡29-30።
2. የመሰየም ሂደት ቁልፉ ትንሣኤ ነው፣ ይህም ትንሣኤ እንደሚያስነሣው መንፈስ፣ እንደሚሰይመው መንፈስ፣ እንደ የሕይወት ኃይል በመንፈሳችን ውስጥ ያለው በውስጣችን የሚያድረው ክርስቶስ ነው—ዮሐ. 11፡25፤ ሮሜ 8፡10-11፤ ሐዋ. 2፡24፤ 1 ቆሮ. 15፡26፤ 5፡4፦
   - ሀ. እንዴት በመንፈስ መመላለስ፣ የሚሰይመውን መንፈስ መደሰት እና መለማመድ እንዳለብን በአስቸኳይ መማር ያስፈልገናል—ሮሜ 8፡4፣14፤ ማቴ. 14፡22-23፤ ማር. 1፡35-38፤ መዝ. 62፡8፤ 102 ርዕሱ።
   - ለ. መንፈስን አብልጠን በነካን መጠን፣ ለክርስቶስ አካል ግንባታ አዲሲቱን ኢየሩሳሌም ለማጠናቀቅ በሕይወት እና በባሕርይ ተመላኪነቱን ሳይጨምር አምላክ እንሆን ዘንድ አብልጠን እንቀደሳለን፣ እንለወጣለን፣ የልጁን መልክ እንመስላለን እና እንከብራለን—1 ቆሮ. 12፡3፤ ሮሜ 10፡12-13፤ 8፡15-16፤ ገላ. 4፡6።

መ. በሕይወት አብልጠን ባደግን መጠን እና በገንባፍራሽ ቅንባሮ የልውጠት ሂደት ውስጥ ባለፍን መጠን፣ አብልጠን የእግዚአብሔር ልጆች ሆነን እንሰየማለን—2 ቆሮ. 3፡18፣ 6፣ 16፤ 5፡4፣ 9፣ 14-15፤ 1፡12፤ 12፡7-9፦

1. ይህ የገንባፍራሽ ቅንባሮ ሂደት እግዚአብሔር ወደ ሰው ውስጥ በመገንባቱ እና ሰው ወደ እግዚአብሔር ውስጥ በመገንባቱ የቤተ ክርስቲያን እንደ የክርስቶስ አካል እና እንደ የእግዚአብሔር ቤት መገንባት ነው—ሮሜ 12፡2፤ ኤፌ. 1፡22-23፤ 2፡20-22።
2. ሰብዕና በመለኮት ውስጥ ተሰይሟል፣ መለኮትና ሰብዕና ደግሞ በአንድ ላይ ተዋሕደዋል፤ ዛሬ የሰብዕና ዘሮች የሆንን እኛ በእግዚአብሔር የግንባታ ሂደት በኩል በመለኮትነት የእግዚአብሔር ልጆች እየሆንን ነው—ማቴ. 16፡18፤ ኤፌ. 3፡16-19፤ ራእ. 21፡2፣ 9-10።
3. በልቡ መሻት መሠረት የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ እና ግቡ ራሱን ወደ ሰው ውስጥ መገንባት እና ሰውን ወደ እርሱ ውስጥ መገንባት ናቸው፤ ይህ ግንባታ እንደ ታላቅ፣ ብዙዎች እንደተካተቱበት አምላክ-ሰው፣ እንደ የእግዚአብሔር ልጆች ጥቅል-ድምር በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ይጠናቀቃል—ቁ. 7።
4. አንድ ቀን ይህ ሂደት ይጠናቀቃል፣ ለዘላለምም ከክርስቶስ፣ ከእግዚአብሔር በኩር ልጅ ጋር በመንፈሳችን፣ በነፍሳችን እና በሥጋችን አንድ አይነት እንሆናለን—1 ዮሐ. 3፡2፤ ሮሜ 8፡19፣ 23፤ ከእንግሊዝኛ የመዝሙር መጽሐፍ ቁጥር 948፣ ሁለተኛ የግጥም ስንኞች።

ሠ. በእግዚአብሔር በኩል፣ ሦስታንዱ አምላክ ሰው ለመሆን ሥጋ ለብሷል፤ በእኛ በኩል፣ ለዘላለም የእርሱ ብዙዎች የተካተቱበት መገለጥ እንሆን ዘንድ በሕይወት እና በባሕርይ ተመላኪነቱን ሳይጨምር አምላክ እንድንሆን መለኮት

እየተደረግን፣ በሂደት ባለፈው እና በተጠናቀቀው ሦስታንዱ አምላክ እየተቀናበርን ነው፤ ይህ ከፍተኛው እውነት ነው፣ ይህ ከፍተኛው ወንጌል ነው።

**V. የሕይወት-ጥናቶች መጽሐፍትን እና የሪከቨሪ ቨርዥን መጽሐፍ ቅዱስን የግርጌ ማስታወሻዎች በመጠቀም በእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ ከፍተኛ እውነት መቀናበር እና እውነቱን ማሰራጨት ያስፈልገናል፤ የሕይወት-ጥናት መጽሐፍት እና የሪከቨሪ ቨርዥን መጽሐፍ ቅዱስ የግርጌ ማስታወሻዎች ሕይወትን ለማገልገል፣ እውነትን ለመልቀቅ እና የመጽሐፍ ቅዱስን መጽሐፍት ለመክፈት ናቸው—ኢዮብ 10፡13፤ ተዛ. ኤፌ. 3፡9፡-**

ሀ. የጌታ ምለሳ የእውነቱ ብርሃን ምለሳ ነው፤ ዛሬ በምድር ላይ ያለው እጅጉ አስቸኳዩ ፍላጎት የዚህ ዘመን እውነት ነው፡-

1. የሕይወት ጥናት መጽሐፍት ከሪከቨሪ ቨርዥን መጽሐፍ ቅዱስ እና ከግርጌ ማስታወሻዎቹ ጋር መጽሐፍ ቅዱስን ለእኛ ለመክፈት ዋነኛ ቁልፎች ናቸው፤ መጽሐፍ ቅዱስን እንዲተኩ ሳይሆን ሰዎች ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዲያመጡ ነው—ሐዋ. 8፡26-39።
2. የሪከቨሪው ቨርዥን መጽሐፍ ቅዱስን ጽሑፍ ከግርጌ ማስታወሻዎቹ ጋር እና የሕይወት-ጥናት መጽሐፍትን ጸሎት ለተሞላበት ጥናት እንደ የጥናት መጽሐፍት መቁጠር አለብን፤ እንዲሁ ቀላል በሆነ መንገድ ካነበብናቸው ጊዜያዊ የሆነ ምግብና መነቃቃት ብቻ እንቀበላለን፤ ያነበብነው አብርሆት በተሰጠው ትውስታችን እውነት ሲሆን የማያቋርጥ እና ዘላለማዊ ምግብ ይሆንልናል—መዝ. 119፡130።
3. የሕይወት ጥናት መጽሐፍት መልእክቶች ውጥናቸው እና ግባቸው ውድ መዝገቦችን ቆፍረን እናወጣ ዘንድ የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት "የማዕድን ስፍራውን ለመክፈት" ነው፤ "እውስጣቸው ለመግባት ዓመታትን ማጥፋት ከእናንተ የሚጠይቁ ብዙ ነገሮችን አሳትሜአለሁ"—ከ*The Collected Works of Witness Lee, 1984*, vol. 2. "Elders' Training, Book 3: The Way to Carry Out the Vision" ከሚለው መጽሐፍ ከገጽ 316 የተወሰደ።

ለ. የተተረጎሙትን፣ ፍቺ ያገኙትን እና ወደ መረዳታችን የመጡትን መለኮታዊ እውነቶች ለጌታ ምለሳ ለማሰራጨት ዛሬ ኃላፊነቱን መሸከም አለብን፡-

1. መለኮታዊዎቹን እውነቶች እናጠና፣ እንማር እና እናሰራጭ ዘንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ተገቢ መረዳት በጽሑፎቻችን ተሰባስበዋል፤ የሪከቨሪው ቨርዥን መጽሐፍ ቅዱስ እና የግርጌ ማስታወሻዎቹ ባለፉት ሁለት ሺህ ዓመታት በሁሉም ስፍራ የነበሩ ቅዱሳን የደረሱባቸው የመለኮታዊው መገለጥ መረዳት "ንጥር" ናቸው።
2. ጌታ እነዚህን ውድ እውነቶች ለክርስቲያኖች ብቻ ሳይሆን ለማያምኑት ሰዎች እንኳን እንድናሰራጭ ሰጥቶናል፤ ዛሬ ጌታ የሚያስፈልገው ነገር እርሱን የሚወዱት፣ ለእርሱ የሚኖሩት እና ከእርሱ ምለሳ ውጭ ምንም የማያውቁት ውድ የሆኑት በሺዎች የሚቆጠሩት ቅዱሳኑ እነዚሁኑ እውነቶች ያሰራጩ ዘንድ እነርሱን ለጌታ ሕዝብ በተገቢው ጊዜ ምግብ የሚያቀርቡ ታማኝና ልባም ባሪያዎች ለማድረግ አንድ መንገድ ይወስዱ ዘንድ ነው፤ ያኔ የጌታን ምለሳ ተልዕኮ እናሟላለን—2 ቆሮ. 5፡14-15፤ ማቴ. 24፡45።
3. የቤተ ክርስቲያን መጨመር በእውነት መሰራጨት ላይ ይመረኮዛል፤ እውነቱ ብቻ ሰዎችን ማሸነፍ እና ማግኘት ይችላል፤ ለቤተ ክርስቲያን መባዛት እና መሰራጨት ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ሁላችንም የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ ኢኮኖሚ እውነት ለመማር እና ክርስቶስን ለሌሎች ለማገልገል ጊዜ ማጥፋት አለብን—ሐዋ. 6፡7፤ 12፡24፤ 19፡20።

*© 2021 Living Stream Ministry*